# ማን ያውቃል?!



የአዶልፍ ሂትለር ሃሳብ - ውስጣዊ ግምቱ፣
ብረት ጦሩን ሰብቆ - ሠራዊት ማዝመቱ፣
ዓለምን ለመግዛት - ነበር ውጥን ህልሙ፣
አልገመተም ነበር ነገውን አሻግሮ...
እስኪሰበር ቅስሙ::



በፋሽስታዊ ግፍ - ኢትዮጵያን በመውረር፣
የተስፋ ምኞቱን - ከመደስኮር በቀር፣
አንዲት ቀን ስትከዳው - ፍዳ እንደሚከተል፣
ባፍጢም ተዘቅዝቆ - እንዳለ መሰቀል፣
በሕይወት ዘመኑ - አልተረዳም ነበር፣
ዱቼ ሙሶሎኒ - ሲከንፍ በሃሳብ ሰካር::



በዚያ በኩራቱ - በዚያ በትቢቱ፣
ላያሌ ዓመታት - ኢራቅን መግዛቱ፣
የወርቅ ብረት አጥር - ከቶ እማይበገር፣
ፍጻሜ የሌለው - ዘላለማዊ ክብር፣
መስሎት ነበር ሳዳም - ያቺን ዕለት ሳያውቅ፣
ባንዲት ቀጭን ገመድ - አንገቱ እስኪሸመቅ::



«ጓድ!» እንደተባለ - አብዮታዊ መሪ፣
ለዘላለም ዓለም - በአጀብ ደምቆ ኗሪ፣
ይመስለውም ነበር - ኮሎኔል መንግሥቱ፣
የቁርጥ ቀን ደርሳ - እስኪታይ ስደቱ::



ማኅደሩን ታቅፎ አሻፈረኝ ብሎ ከታሪክ ለመማር፣
በጨለማ ሕይወት ጥላውን በመፍራት ተሸማቆ ሲኖር፣
በብረት ተከቦ በምኞት ፈረሱ ከመጋለብ በቀር፣
በእልህ ጭካኔ ከፊቱ ያገኘውን ከመጨፍጨፍ ሌላ፣
ለልጆቹ ዕጣ ለራሱ መፃዒ አይቀምርም መላ፤
የጭካኔ ክንዱን ሕዝብ ላይ ያሳያል፤
የሕዝብ ልጆች ላይ ገምድሎ ይፈርዳል፤
መቼም እንደምንም የጭፍን ድንብሩን ዛሬውን ይኖራል፤
ቀን የከዳች ዕለት ነገውን ማን ያውቃል?!

ጌታቸው አበራ

ሰኔ 1999 ዓ.ም. (2007)